# ሸሙጥ

## እንዳመቻች የምትወጣ ነፃ ጋዜጣ

**ቁጥር** 1 **ጥር** 5 **ቀን** 1968 **ዓ.ም.**

*ይድረስ*
*ለልዑል ጌታየ መርእድ አዝማች አስፋወሰን ሃይለ ስላሴ*
*ከአንድ ባሪያዎ*

*ከሁሉ አስቀድሜ ልዑልነትዎን በየማነሃይል አቁሞ፣ የጀመሩትንም እንዲፈፅሙ አድርጎ፣ በዚች በክፉ ጊዜ ፈቃዱ ሆኖ ከሃገር እንዲወጡና አባትዎ ዝናና ክብር በተጎናፀፉበት በሃገረ  ብሪታንያ በጠቢባን ሃኪሞች ተከበው እንዲቀመጡልን ለአደረገ የእስራኤል አምላክ ክብር ምስጋና ይግባው። ይቺ ደብዳቤ ስትደርስዎ አሁንም በሃገረ ኢትዮጵያ ልዑል የሚለኝ አለ ወይ ብለው ይገረሙ ይሆናል። አወን አለን። ቁጥራችን ቢያንስ አጥንታችን የጠራ፣ ደማችን የነፃ ስለሆንን ይህን የድሃ ልጅ ሁሉ ከቅንጣት ጤፍ አንቆጥረውም። እነርሱ ሊያዛንቁን ቢፈልጉም ጥራታችንን እንጠብቃለን። ነፍሳቸውን ይማርና ወይዘሮ ማንአለብሽ የኢትዮጵያ ህዝቦች ከአምስት መቶ አንበልጥም ይሉ ነበር። እርሳቸው ባይማሩና ቁጥር ባይለዩ ነው እንጂ ጌታየ የልዑልነትዎ ትክክለኛ ዜጎች ከመቶም አንበልጥ።*

*የእስራኤል አምላክ ዛሬማ ፈቃዱ ሆኖ ሰፊው ህዝብ የሚሉ ፈሊጥ ያሰማናል። ሁሉም እኩል ነው ሊሉን ተነሱ። የኢትዮጵያ አምላክ፣ የኢትዮጵያ አንበሳ የሚልም ንግግር አልፎ አልፎ ይሰነዘራል። ይህ ሽክላ ሰሪና ምናምንቴው ሁሉ ከልዑል ጌታየና ከእኛ ከባሮችዎ እኩል ነኝ ሊል ነው እኮ። ከሰለሞን ከዳዊት የተወለደው "ሞአ አንበሳ ዘእም ነገደ ይሁዳ" ብሎ መፅሃፉ የጠቀሰለትና የጎረደማኔ ልጅ ሰጠኝ አንድ ናቸው ለማለት ነው። ውሃ አሻቅቦ ይፈሳል የተባለው ደረሰ። ይህን ሁሉ ጉድ ያላሳየዎት አምላክ ይመስገን። እርስዎና መኳንንቶችዎን በሃገረ ብሪታያ አስቀምጦ ከዚህ ሁሉ ጉድ የሰወራችሁ ጠብታም ትሁን የእስራኤል ደም ስላላችሁ መርጧችሁ አይደል? እኔም በአቤቶ ባህሪይ የሳህለ ስላሴ ልጅ እንደ መሆኔ መጠን የእስራኤል አምላክ ይጠብቀኛል።*

*ነብይ በሃገሩ አይከበርም እንዲሉ ሆኖ ነው እንጂ ጌታየ ፊቱኑ ተናግሬ ነበር። ይኸ በሸምብራ ጥላ የሚውል ተማሪ ሁሉ መሬት ለአራሹ የሚል ፈሊጥ ሲጀምር በየአደባባዩ አስር አስሩን መስቀል ነው፣ ጉድ አንድ ሰሞን ነው ብል የሚሰማኝ አጣሁ። ነፍሳቸውን ይማርና ልዑል አስራተ ካሳም አስር ይበዛል አንዱን መጦለብ ነው ቢሉ ማን ይስማ? ይኸው እሳቸውም የሆኑትን ሆኑ። ግድ የለም፣ ደም ይደርቅ መስሏቸው!*

*እንደተፈራው ሆነና ለቤት ቡና ትሆነኛለች ብየ ጅማ ያለማኋትን ሃያ አምስት ጋሻ መሬት፣ ለቤተ ሰቤ ቀለብ ይረዳኝ የነበረውን ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል የወረስኩትን አስራ ሁለት ጋሻ መሬት፣ ከአቤቶ ባህርይ ሲወርድ ሲዋረድ የደረሰኝን ዳማ ከለለኝም ባይሆን ለቤት ጠላ ይሆነኝ የነበረውን የሰላሌ የገብስ መሬት በሙሉ ቀሙኝ። ይህስ ባልቆጨኝ ነበር። በዚህ በአምቦ መንገድ የአባቴ አሽከሮች ተክለውት የእነርሱ ማስታወሻ ነውና ለማገዶ እንጂ አልነካውም ብየ ያስቀመጥኩትን አንድ ጋሻ የባህር ዛፍ መነጠቄ ነው የአንገበገበኝ። ልዑል ጌታየማ የሰጡኝ የጨፋው አስር ጋሻ ገና ሳይታወጅ እኮ ነው ይኸ የድሃ ልጅ ሁሉ መሬቴ ነው ብሎ የወሰደው። የባለቤቴንም መኪና ጃንሆይ የደጃዝማች ውብነህ ልጅ በእግሯ አትሄድም ብለው የሰጧትን ወሰደባት። በዛሬ በርበሬ መወደድ የማረቀውም አንድ ጋሻ መሄድ ይሰማኝ ጀምሯል። ዘረፋም አይደል? ተሻሙበት።*

*እንዳሰብነው ሁሉ ጌታየ ገስግሰው አዲስ አበባ ሲገቡ ይሄ አልሰሜ ቀማኛ ሁሉ የሚገባበትን እናያለን። ደም ቢያለቅስ ድንጋይ ቢነክስ አይቀር። የውጭውንስ ይውሰዱት፣ ልጆቹም አልፈለጉት ብየ ነበር። የጉለሌ ሶስት ቤቶቼ እስከተከራዩና የፒያሳው አስር ደጃፍ እስከአለ ድረስ ያቺን የእለት ጉርሴን አላጣትም ብየ ነበር። እድሜ ለልዕልት እመቤቴ፣ የአባታቸውን ሃዘን ያቅልላቸው እያልኩ የአዲስ ከተማ በረንዳዎቼን ኪራይ ለቤት ቡና ያህል አውል ነበር። ምን ይሆናል! ምን ይሆናል ጉግ ማንጉግ አህዛብ እርሱ ፈቃዱ ሆኖ አመጣብን። በሃዘንዎ ላይ ሃዘን አልጨምርብዎትም የጃንሆይን ነገር አላነሳም። እንበቀላቸዋለን።*

*ስለ መምጣትዎ የአፈንጉስ አጥናፉን ልጅ መንፈቅ ይሆናል ጠይቄው ነበር። ወግ ጠራቂ፣ ታሪክ አዋቂ፣ የወሬ ቋት ስለሆነ ለጣልያንም አሳባቂ ነበር። ከዚያም የመኮንን ሃብተ ወልድ  ዞሮ ነበር። መቼ አጡት ጌታየ። ታዲያ ዛሬም ለደርጎቹ ይቀቅራል። ሥጋ ነውና አይሸጠንም ብየ ነው። ታዲያ እርሱ ነው መሰል እርሳቸውም አልተሻላቸውም፣ ገንዘብም ይቸግራቸዋል አለኝ። ይህንን ስሰማ ቅር ብሎኝ እህልም አልበላ ብሎኝ ከርሜ ነበር። እሱማ የሚያወራው ብዙ ነው። የራስ መስፍን ልጆች ወደ ሽቀላው ገብተዋል፣ የሃይለ ማርያምም ልጅ መልከ ቀና እንደመሆኗ /ከአፈር ይሰውራት ጌታዬ/ ፈረንጁም አፍሪካውም እያስቀመጣት ነው እንጂ የሎንዶን ኑሮ ለመኳንንቱ እጅግም አልረባቸው ይለኛል። የእሷ እንኳን እጅግም አልገረመኝም። እናቷ ወይዘሮ ሸዋንግዢው ደማቸው ፍልቅልቅ ያለ ቆንጆ ነበሩና በጠላት ዘመን ጣልያን ይወዳቸው ነበር። አልመስል ያለኝ የመኳንንቱ መቸገር ነው።*

*ኮለኔል ጀማነህ በላቸው ከመሄዱ በፊት ልዑል ጌታየ የጨፋ ገንዘብ እንደሚላክልዎት፣ ቀደም ብሎም ጥቂት ሚልዮን መቀመጡን የአፈ መስፍን አንዳርጋቸውና የፀሃፊ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስም እንደማይጠፉ ነግሮኝ ነበር። ወልደ ጊዮርጊስ እንኳን እናንተ አነሳችሁት እንጂ ጠፍር ነካሽ መሆኑን እናውቃለን። የአንዳርጋቸውም ዝኒ ከማሁ ነው። የድሃ ልጅ ምንጊዜም መንፈሰ ድሃ ነውና የጋራ ጥቅማችንን ይስተው ይሆናል።*

*የእነሱ ቢቀር እንዴት የውጮቹ አይረዱንም? በላቸው ሲነግረኝ አሜሪካኖቹ በርቱ ብለውናል። በሳውዲ አረብና በሱዳን በኩል ጠመንጃ እናቀብላለን ብለዋል። ደርጉም ውስጥ ሲሳይና የኋላሸት የሚባሉትንና  አንዳንድም የኮሚቴ መሪዎች እንደ ንብ ቀስመው፣ እንደ ወጥ ቀምመው እስከ ስምንት አመት ድረስ አሜሪካን ልከው ያሰለጠኗቸው አሉ ብሎ ነበር። ታዲያ ይህ ከሆነ እሱስ ምን አስኬደው? እዚሁ ሆነን ሁሉንም እንመክርበት ነበር። የሱን ስራ ለመናቅና ለማንቋሸሽ ሳይሆን /ብዙ ትልቅ ስራ እንደ ሰራ አውቃለሁ/ ችግሩን ለመግለፅና መላ ለመምታት ነው። ይንቀላቸውና ነቀሉት እንጂ ከመልቀቁ በፊት በየአውራጃውና በየ ወረዳው የአስቀመጣቸው የኛ ሰዎች ብዙ እየረዱን ናቸው። ዓለማየሁ የሚሉት ፖሊስ እሱ እስካለ ድረስ ረድቶን ነበር። ትንሽ ስጋ እንደ መርፌ ትወጋ እንደሚባለው ልፍስፍስም ቢሆን የራስ እምሩም ልጅ አለ። እነ ዶክተር አስራት፣ እነ ዶክተር አክሊሉ የኛው ልጆች ናቸው። በምክትል ሚኒስትርነትም የፊታውራሪ በኩረን ልጅ ልጅ እንዳልካቸው እንዳስቀመጠው ይኸው አጥብቆ ይዝዋል። ሌሎች እንዳልካቸው የሾማቸውም ሚንስትሮች ችሎታ ያንሳቸዋል እንጂ በእኛ አይጨክኑም። በእንደራሴነትም /አሁን ማንትስ ብለዋቸዋል/ ሸዋም፣ ጎጃምም፣ በጌምድርም፣ ሐረርጌም ያሉት አይከፉም። ሲዳሞም ያን የዲያቢሎስ ዝርያ ሻለቃ ተፈራን አስነስተን ለኛ የሚበጁንን ተክለናል። ጅማም የአባ ጂፋርን ልጅ ሾመው ያንን የእግዜር ሰው ዶክተር መኮንንን ቢያስቸግረው እንዲነሳ አደረግን። ትዝ አይልዎት እንደሆን እንጂ የእኔን ትንሹን ልጄን ከአለማያ ተመርቆ አሜሪካ ሲሄድ ጫማ እንዲስም አምጥቼው ነበር። ዛሬማ ዶክተር ሆኖ አዋሽ ውስጥ ይሰራል። እሱና ባልንጀሮቹ እነ ዶክተር አስራት፣ እነ ዶክተር ባንታየሁ ከደርጉ ጋር ደህና እየተገናኙ ዋና ዋና ቦታዎችን በማስያዝ ይረዳሉ።*

*በላቸው ቢሄድ ማህረ ምንዳና አጥናፉ አሉ። ንጉሤ የሚባለውን ፀጥታ በላቸው አስተዋውቆኝ ነበር። የአጥናፉ ቀኝ እጅ ስለነበረ ብዙ ረድቶን ነበር። አድሃሪ እያለ ብዙ ተቃዋሚዎችን እንዲያሳስር ተነጋግረን ዶባስ የተባለውንም ወዳጁን አስተዋውቆኝ ነበር። አድሃሪ ማለት ጌታየ አዲሱ ቋንቋ ነው።ወዛም ገማህ ቢለው የነጭ ወሬ ነው እንዳለው ዱር አዳሪ፣ በረንዳ አዳሪ ሁሉ እኛን አዳሪ ይለን ገባ። እነ ንጉሤማ ጌታየ አልቆዩም ተያዙ። ቢሰጧቸው የማይጠግቡ ዥቦች በመሆናቸው እኔም ጨንቆኝ ነበር። የጠላ ጠላ ወሬ እንደ ደረሰኝማ አጥናፉም ያሰጋዋል ተብሎ ነበር። ይኸው እስከዛሬ ቆየ። አንድ ዛጎል ጣይ ቢጤ መለኛ ከደብረ ማርቆስ መጥቶ እኔ ዘንድ ተቀምጦ አጥናፉን ይገናኘው ነበር። በሱ በኩል ደህና ሰርተን ነበር።*

ሆኖም ጌታየ ነገሩ በሹመት ብቻ አይሆንም። በሌላውም ቶሎ ቶሎ ማለት ነው። እነዚህ ጉግ ማንጉጎች እንደማያዋጧቸው ለአሜሪካኖቹም መንገር ነው። ሽመልስማ ለድርቅ እያሉ ይረዳሉ፣ እጃቸው ባይወጣ ይሻላል ይለናል። ብቻ እነ ሽመልስ እንደ አሜሪካኖቹ በሁለት ቢላዎ የሚበሉ ናቸው። ርስታችን ከሄደ እኛ እንደሌለን አይገባቸውም። በደንብ ይመከርና ውጭ መንግስት ይቋቋም። እዚህ ያለውን እኛ እናስተባብራለን ብለን ደህና ጀምረን ነበር። እንዲረዱ፟ችሁም በክፍሌ ወዳጆና በሻምበል ሲሳይ በኩል የነቁ የተቡ ትጉዕ ልጆች አምባሳደር እየሆኑ እንዲሄዱ አድርገን ነበር።

በውጊያውማ ሃይሉ ረጋሳም፣ እነ በሻህ ውረድም፣ የራስ ብሩ ልጆችም ደህና ጀምረው ነበር። ጦር ሲላክባቸው ከደርግ እየተነገረን እየጠቆምን ጠንክረው ነበር። ምን ይሆናል ሁሉም ከዷቸው። ሲዳሞም፣ አዚህ ዝዋይም፣ ግንደ በረትም በየቦታው ተፋፍሞ ነበር። ብዙ ጀግና አለቀ። የግንባር ሥጋ ሆነ። አንቺማ ታቦኪያለሽ ውሻ ይደፋብሻል እንጂ እንደሚባለው ሆኖ አስቸገረን። እርዳታ ከውጭ አግኝተን ቢሆን፣ ፈረንጆቹም ቀድመው ተይዘው ቢሆን ኖሮ ስንት በተሰራ ነበር። ሁሉም በገንዘብ ነው።

የአለፈው አልፎ ክፉው ቀን ወደ ማለቂ ደርሶ፣ ዛሬ ህብረት ተብሎ ድርጅታችን መቋቋሙ ትልቅ የምስራች ነው። ለነጋ ተገኘ በጌምድር አያቅተውም። ጋይንትም ተደብድቧልና ደሙን ይበቀላል። አርማጭሆ የገባንስ ማን ይደፍረዋል? ጎጃምም ጎጃም ነው። በዚያ በኩል አባታችን እንዲረዱ ይደረጋል። የልዑል ራስ መንገሻንም ስም በትግሬ እንዲአሟሙቁ አድርገናል። ጀኔራል እያሱ የኤርትራን ጉዳይ ካጠበቀ ለአሊ ሚራህ ልዑል ጌታዬ አሉ። አዳል ይቀበለዋል። ብርሃነ መስቀል ላስታን ይዟል። ወሎም ይከተላል። ሌላ ሌላውም ለጊዜው ቢያስቸግረንም ታረቁ ብለን ያስገባናቸው ወገኖቻችን ጊዜው ሲደርስ ይወጣሉ። ሱማሌን አነጋግሮ በውጋዴን እንድትገፋ፣ በኤርትራም አስመራንና አሰብን እንዲያጠቁ ከተደረገ እነሱ ሲደናበሩ ጎንደርን መያዝ ይቻላል። የጅማም ገዥ የኛው ስለሆነና ማህበር የሚሉትን ስላጠፋልን የሚቀለው ከጎንደር ቀጥሎ ጂማን መያዝ ነው። ከዚያ ጌታየ ገበሬ ማህበር የሚሉት ምሳር ይዞ ይውጣ እንቆላዋለን። በኬንያ በኩል የውጭ ጦር ቢጨመርማ ይሄን ደራሣና ሌላ ምናምንቴ ደርግ ያድነው እንደሆነ እናይ ነበር። የሚሮጥበት ሜዳ፣ የሚገባበት ቀዳዳ፣ የሚመክተው ጋሻ፣ የሚሰወርበት ዋሻ እናሳጣው ነበር።

በከተማም ጌታዬ አያያዙ ክፉ አይደለም። መሬት ላራሹ ሲል የከረመው ዘመቻ ብሎ አንድ ሰሞን በየገጠሩ ውር ውር ብሎ ነበር። የአያትን አየና መለስ አለ። በከተማም የኛኑ ቤት አከፋፍል ተብሎ ነበር። አልመሰለኝም እንጃ። በደርጉ በራሱ ላይ ዞረበት። ነገሩ መቼም እንዲሁ አልመጣም። ጠሊቅ ዘሊቅ ምስጢር አለው። እንደምንም ብለን የልጅ ልጆቻችንን መካከላቸው አስገብተን እንደ አለሌና እንደ ባዝራ፣ እንደ ዘይትና እንደ ወይራ፣ እንደ ንፍሮ እህል ተቀላቅለው፣ ከነሱ ይበልጥ ኮሙኒስት መስለው እንዲገቡ አድርገናል። ስራው እየተሰራ ነው አይጨነቁ ጌታዬ። ይሄ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት /ሲቪሉ ጌታዬ/ ክረምትና በጋን አንድ ወገን የሚያደርግ፣ ሳይዘንብ ከአመት አመት የእህል በረከት የሚያወርድ፣ ቅቤና ማሩ ጣዕሙ የሚጨምርበት፣ ወርቅ ልዑል ጌታየ ወርቅ የሚታፈስበት፣ ዓመቱን ሙሉ ሳይዘራ፣ ሳይታጨድ፣ ሳይወቃ የሚበላበት ፣ መቼም ድረስ ያልፋል ይጠፋል ያልቃል ይደቃል የማይባልበት ምድራዊ መንግስተ ሰማይ አድርጎ ሲያቀርበው እኔንም ይነሽጠኛል። ቁም ነገሩ ግን ጌታዬ የነሱ መንግስት ሳይሆን ይሄን ተማሪ ወደ ከተማ መመለሳቸው ነው። ትፈሳ ዶሮ የሌለው ገበሬና ተማሪ ሲገጥም ደግ አይደለም። እዚሁ ከተማ ፋሽሽት ፋሽሽት ቢልልን ይሻለናል። ግን እኮ ውነታቸውን ነው ጌታዬ። ፋሽሽት ነው። ጣልያን ምን አደረገን? መሬት አልቀማን። እንዲህ አላዋረደን። ደሞ የፖለቲካ ፅ/ቤት ብሎ አጋንንት ሰብስቧል። ብቻ ግድየለም። ነገሩን ማስቀረት ቢያቅተንም የባላምባራስ ገዳሙን ልጅ፣ የራስ እምሩን ልጅ፣ ሻምበል ሲሳይን ከበላይ አድርገናል።

እንግዲህ ልዑል ጌታዬ በኛ በኩል ያለው ይሄ ነው። ሶርያዊው ቅዱስ ጊጋር እመቤታችንን እንደሸሸገ ሁሉ የሸሸግናቸው ወገኖቻችን በቶሎ ለመመለስ ያብቃቸው። ዘር ትበደር ሂዳ እህል ሲሸት መጣች እንዳይሆን መጠንቀቅ ነው። ለፖለቲካው ለንደን ጥቂት ሰው ይበቃል። አነጋገራቸው የሚያስደነግጥ ልጆቻችንንም አትሸሿቸው። እዚህ ካሉት ጋር አብረን ደርግን ለመጣል መስማማት- ችለናል። ልጓም ለቆ ቼቼ እንዳይሆን ጠበቅ አድርጎ መያዝ ነው። ማብላት ነው።

ባሪያዎ ለጥይበሉ ድፋባቸው።